የሰ.መ.ቁ.177968

መስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
2. ቀነዓ ቂጣታ
3. ፈይሳ ወርቁ
4. ደጀኔ አያንሳ
5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካቾች፡-1. የናዝሬትና አርሲ ሳሙና ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ⎫ ነ/ፈጅ ባህር
2. ናዝራዊ ቅባ-ኑግ ኃዋየተ/የግ/ማህበር ⎭ ጠይቦ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ሚሊዮን መኮንን
2.አቶ ዮሐንስ ዓለሙ
3. አቶ ፀጋዬ ዓለሙ
4. አቶ ተፈሪ ዓለሙ ⎬ ጠበቃ ሀብታሙ አበበ ቀርበዋል፡፡
5. አቶ ዳንኤል ዓለሙ
6. ወ/ሪት ሔለን ዓለሙ
7. አቶ ቅዱስ ዓለሙ
8. አቶ ሚኪያስ ዓለሙ
9. ወ/ሮ የሺ አለማየሁ - የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍ ር ድ

ይህ የማህበር አበልነት ክርክር የተጀመረዉ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካቾች የሥር ተከሳሾች፣ የአሁን ተጠሪዎች የሥር ከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካቾች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.169919 በ12/07/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካቾች በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ እነዚህ ሁለቱ የተከሳሾች ፋብሪካዎች/ማህበራት በሁለት ግለሰቦች አቶ መኮንን አባተ እና አቶ አለሙ ገብሩ የተመሰረቱ ሲሆን፣ ከዚህ ቀደም አቶ መኮንን አባተ በመሞታቸዉ ወራሾቻቸዉ 16 ሰዎች ወራሽነታቸዉን አረጋግጠዉ በፋብሪካዎቹ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት በአባልነት የተመዘገቡ ሲሆን፣ ቀጥሎ አቶ አለሙ ገብሩ በመሞታቸዉ 1ኛ ከሳሽ ወ/ሮ የሺ አለማየሁ ሚስትነቴን እና ከ2ኛ-9ኛ ያሉት ከሳሾች የሟች አባታችን አቶ አለሙ ገብሩ ወራሾች መሆናችንን በወረዳዉ ፍ/ቤት አረጋግጠን፣ ሟች በእነዚህ ፋብሪካዎች [ማህበራት] የነበራቸዉን የአክስዮን ድርሻ በስምምነት ተከፋፍለን በእያንዳንዳችን የአክስዮን ድርሻ መሰረት በአባልነት እንዲንመዘገብ ብንጠይቅም በጋራ አንድ ሰዉ

ካልወከላችሁ በስተቀር ለየግላችሁ ሊትመዘገቡ አትችሉም በማለት ሊመዘግበን ስላልቻሉ፣ በንግድ ሕጉ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት እያንዳንዳችን የአክስዮን ድርሻ መሰረት በአባልነት እንዲንመዘገብ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል። ይህን ክርክራቸዉን ለማስረዳት ማስረጃ አያይዘዉ ማቅረባቸዉን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል።

የሥር ተከሳሾች በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት መልስ የከሳሾች የዳኝነት ጥያቄ ሲታይ በንግድ ሕግ አንቀጽ 328 እና በማህበራቱ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 4 [2] መሰረት ከሳሾች አንድ ሰዉ በመወከል የተከሳሾች ማህበራት አባል መሆን ይችላሉ እንጂ እያንዳንዳቸዉ አባል ሊሆኑ አይችሉም፤ አሁን በሥራ ላይ ያለዉ የመተዳደሪያ ደንብ ሆነ የንግድ ሕግ አንቀጽ 524 ድንጋጌ የከሳሾችን ክርክር የሚደግፍ አይደለም፤ የአቶ መኮንን አባተ ወራሾች በመጀመሪያ መተዳደሪያ ደንብ በእያንዳንዳቸዉ አክስዮን ድርሻ አባል እንደሆኑ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለዉም፤ ከሳሾች የዉርስ ንብረት ክፍፍል አድርገን ቃለ ጉባኤ በፍ/ቤት ዉሳኔ ተሰጥቶበታል ይባሉ እንጂ ዉሳኔዉ ተሽሯል። ስለሆነም ከሳሾች ያቀረቡት ክስ የሕግ ድጋፍ ስለሌለዉ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት መከራከራቸዉን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል። ይህን ክርክራቸዉን ለማስረዳት የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዘዉ መቅረባቸዉን መዝገቡ ያሳያል።

ከዚህ በኋላ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከርና የቀረበዉን የሰነድ ማስረጃዎች በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ እኒዚህ የተከሳሾች ፋብሪካዎች በመንግስት ተወርሶ በመንግስት እጅ ቆይቶ በ2000 ዓ.ም አቶ መኮንን አባተ እና አቶ ዓለሙ ገብሩ ተገቢዉን ክፍያ ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ከፍለዉ ያስመለሱ ሲሆን፣ አቶ መኮንን አባተ ሲሞቱ ወራሾች 16 ሰዎች በአቶ ዓለሙ ገብሩ ፍላጎት በበፊቱ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት በማህበር በአባልነት የተመዘገቡ ስለሆነ በዚህ ረገድ ከሳሾች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለዉም። እነዚህ ማህበራት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበራት ስለሆኑ ካላቸዉ ልዩ ባህርይ የተነሳ በጋራ ቤተሰብ በሆኑት እና ግንኙነትና ትልቅ አመኔታ ባላቸዉ ሰዎች መካከል የሚመሰረት ስለሆነ፣ የእነዚህ ማህበራት አባል ለመሆን በማህበሩ አባላት እና በመተዳደሪያ ደንቡ በስምምነት እንጂ በሕግ እና በሌላ አካል ዉሳኔ መሆን የለበትም፤ ከሳሾች የሟች አባታቸዉን የአክስዮን ድርሻ በመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 3.1 እና 4.4 መሰረት ለመዉረስ የወራሽነት መብት ያላቸዉ ቢሆንም ይህን መብታቸዉን እንዴት እንደሚጠቀሙ በተመለከተ የማይከፋፈልና የጋራቸዉ ስለሆነ ወራሾች ከ2ኛ-9ኛ ከሳሾች ድርሻ እያንዳንዳቸዉ ተለይቶ የተወሰነ ቢሆንም እነዚህ ማህበራት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበራት በመሆናቸዉና ካላቸዉ ጸባይና አመሰራረት የተነሳ ከሳሾች ወራሾች ስለሆኑ ብቻ በአባልነት የመመዘገብ መብት የሌላቸዉ ስለሆነ በወራሽነት መብት ሊይዙት የሚገባቸዉ አክስዮን ድርሻ መሰረት አንድ ሰዉን ብቻ በመወከል የሚጠበቅባቸዉን የሚያስረዳ ስለሆነ በየግላቸዉ እንመዝገብ በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለዉም፤ 1ኛ ከሳሽ ወ/ሮ የሺ አለማየሁ ሟች ሚስት ስለሆኑ በሚስትነት ድርሻቸዉ ለመጠቀም ሌላ ሰዉ በመወከል ለመጠቀም የሚያስገድድ ነገር የለም ከሳሽዋ የአክስዮን ክፍፍል ድርሻ በኋላ አጣርታ ተላይቶ የሚታወቅ በሁለቱም ማህበራት በቀጥታ ለመሳተፍ መብቷን ማስከበር ትችላለች በማለት ወስኗል።

የሥር ከሳሾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ከሳሾች ሟች አቶ

ዓለሙ ገብሩ በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.996 መሰረት ሚስት 50% እና ወራሾች 50% እንደሚገባቸዉ በፍ/ቤት በተሰጠ ዉሳኔ አረጋግጠዋል፤ ይህ ዉሳኔ አልተሻረም:: ከሳሾች በእነዚህ ማህበራት የሚደርሳቸዉ የአክስዮን ድርሻ የሚስትነት ድርሻ እና ወራሽነት ድርሻቸዉን በስምምነት ተከፋፍለዉ በፍ/ቤት ያጸደቁበት ዉሳኔ የተሻራ መሆኑን የቀረበ ማስረጃ የለም:: የማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 4.4 ወራሾችን የሚመለከት ሳይሆን መጀመሪያዉኑ አባል የሆነ ሰዉ የጋራ ባለአክስዮን ያላቸዉን ነዉ፤ ወራሾችን የሚመለከተዉ የማህበራቱ አንቀጽ 3.1 የወራሽነት ማስረጃ ይዞ የቀረበ ወራሽ ካለምንም ቅደመ ሁኔታ የማህበሩ አባል እንደሚሆን የሚያረጋግጥ ነዉ:: የሥር ከሳሾች የአባታቸዉን የአክስዮን ድርሻ በስምምነት በመከፋፈል እና እያንዳንዳቸዉ በሚደርሳቸዉ የአክስዮን ድርሻ አባል ከመሆን የሚከለክላቸዉ ሕግ በሌለበት፣ የማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ በእነዚህ ነጥቦች ላይ በአጠቃቀሙ መሰረት ያስቀመጡት ነገር በሌለበት እና የንግድ ሕጉ አንቀጽ 328 በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት የሌለዉ ሆኖ ሳለ፣ የሥር ፍ/ቤት ከሳሾች የማህበራቱ አባል መሆን አይችሉም፣ አንድ ሰዉ በመወከል ሊጠቀሙ ይቻላሉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት ነዉ፤ የሥር 1ኛ ከሳሽ ወ/ሮ የሺ አለማየሁ የሟች ሚስት በመሆንዋ ከባለቤቷ ጋር የነበራትን ግማሽ ድርሻ የማትጠቀምበት አግባብ የለም፣ ስለሆነም ሟች በ1ኛ ተከሳሽ ማህበር የነበረዉ የአክስዮን ድርሻ 9,136 ስለሆነ የሥር 1ኛ ከሳሽ የሚስትነት ድርሻዋን 4,568፣ ወራሾች ከ2ኛ-9ኛ ከሳሾች እያንዳንዳቸዉ 571፣ በሥር 2ኛ ተከሳሽ ማህበር ሟች የነበረዉ የአክስዮን ድርሻ 2,900 ሲሆን የሥር 1ኛ ከሳሽ የሚስትነት ድርሻዋ 1,450 ሲሆን፣ 7ቱ ወራሾች ደግሞ እያንዳንዳቸዉ 181 አክስዮኖች፣ አቶ ዳንኤል አለሙ 183 አክስዮኖች ድርሻ ስለሚደርሳቸዉ በዚህ መሰረት በሥር ተከሳሾች ፋብሪካዎች [ማህበራት] አባል እንዲሆኑ በማለት ወስኗል:: ይህ ጉዳይ በይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ በመሰረዝ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል:: የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔና ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ::

የአሁን አመልካች በ22/9/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካቾች የአሁን ተጠሪዎች የአባታቸዉ ወራሾች ሲሆኑ አዉራሻቸዉ የነበራቸዉን አክስዮኖችን ሲወርሱ የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 4 [ሀ፣ ለ፣ ሐ] በሚያዘዉ መሰረት አንድ እንደራሴ በመሾም መሆን እንዳለበት ተመልክቶ እያለ የሥር ፍ/ቤት እንደራሴ መሾም ያለባቸዉ ወራሾች ሳይሆኑ ሌሎች በጋራ የአክስዮን ድርሻ የሚይዙትን እንደሆነ በመተርጎም የሰጠዉ ዉሳኔ የመተደደሪያ ደንቡን እና የንግድ ሕጉን አንቀጽ 328 [1፣ 2] እና 524 [1] ድንጋጌ ጋር የሚጋጭ ነዉ፤ የሥር ፍ/ቤት እነዚህ የፋብሪካዎቹ የመተዳደሪያ ደንቦች ድንጋጌዎች ወራሽ በመሆኑ ሰዎች ላይ ተፈጻሚነት እንደሌላቸዉ አድርጎ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ:: የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤ የሰጠዉ ትርጉም የመተዳደሪያ ደንቡ ለተለዩ ሰዎች የተደነገገ ሳይሆን አንድን አክስዮን በጋራ ለሚይዙ ባለአክስዮኖች በምን ሁኔታ ሊሰሩ እና መብታቸዉን ሊጠቀሙ እንደሚገባ የሚያዛቸዉ ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቱ የሰጠዉ ዉሳኔ ግን የመተዳደሪያ ደንቡን እና የንግድ ሕጉን ድንጋጌዎች የጣሳ ስለሆነ እንዲሻርልን፣ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልን በዚህ ምክንያት የደረሰብን ኪሳራ እንዲከፍሉን በማለት በዝርዝር አመልክቷል::

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣ተጠሪዎች ባላቸዉ የአክስዮኖች ድርሻቸዉ መሰረት አመልካቾች በየራሳቸዉ ይመዝግቡአቸዉ የተባለበትን አግባብ ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 328 እና ከመተዳደሪያ ደንብ አኳያ መጣራት ያለበት ጉዳይ ነዉ፣ በማለት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ10/2/2012 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ የአሁን 9ኛ ተጠሪ የሟች ሚስት እና የተጠሪዎች አባት በአመልካቾች ፋብሪካዎች ያላቸዉን የአክስዮኖችን ድርሻ ወራሾች ስለሆኑ 9ኛ ተጠሪ በሚስትነት ድርሻዋ እና ሌሎች ከ1ኛ-8ኛ ተጠሪዎች በወራሽነት ድርሻቸዉ በሚደርሻቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ በአባልነት እንዲንመዘገብ የሥር የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ምንም ዓይነት የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ ከጠበቃ አበል ጋር እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡
የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና ለቅሬታዉ ምክንያት የሆኑትን ዉሳኔዎች አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን 9ኛ ተጠሪ ባለቤት እና የአሁን 1ኛ-8ኛ ተጠሪዎች አባት የሆኑት አቶ አለሙ ገብሩ የሆኑት የአመልካቾች ማህበራት [ፋብሪካዎች] አባል መሆናቸዉ እና የአክስዮኖች ድርሻ እንዳላቸዉ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ እነዚህ ማህበራት ኃላፊነታቸዉ የተወሰኑ የግል ማህበራት መሆናቸዉም የልተካደ ጉዳይ ነዉ፡፡ አቶ አለሙ ገብሩ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸዉ የአሁን 9ኛ ተጠሪ ሚስትነታቸዉን እና ከ1ኛ-8ኛ ተጠሪዎች የሟች ልጆች እና ወራሾች መሆናቸዉን በፍ/ቤት ያረጋገጡ መሆናቸዉን ከሥር ፍ/ቤቶች የዉሳኔዎች ግልባጭ የሚንገነዘበዉ ነዉ፡፡ የአሁን አመልካቾችም በዚህ ረገድ ክርክር እንደሌላቸዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም በላይ የአሁን አመልካቾች እና ተጠሪዎች ያላከራከራቸዉ ሌላዉ ጉዳይ አቶ አለሙ ገብሩ በሕይወት በነበሩ ጊዜ በአመልካቾች ማህበራት ዉስጥ የነበራቸዉ አክስዮኖች ለተጠሪዎች መተላለፍ እንደሚገባ፣ 9ኛ ተጠሪ የሚስትነት ድርሻ እና ከ1ኛ-8ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የወራሽነት ድርሻ እንደሚገባቸዉ እና መብት እንዳላቸዉ አሁንም ያላከራከረ ጉዳይ ነዉ፡፡ ነገር ግን ግራ ቀኙን ያከራከረዉ ጉዳይ ተጠሪዎች ይህን መብታቸዉን እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸዉ በሚል ላይ ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ የአሁን አመልካቾች እያቀረቡ ያሉት ክርክር ተጠሪዎች መብት ያገኙት ከአንድ የማህበራቱ አባል ከሆኑት ከአቶ አለሙ ገብሩ ስለሆነ በማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ እና በንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት አክስዮኖቹን በጋራ በአንድነት አንድ ሰዉ እንደራሴ ወክለዉ በዉክልና ከሚይዙት በስተቀር እያንዳንዳቸዉ የማህበራቱ አባላት ሆኖ የሚመዘገቡበት አግባብ የለም የሚል ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪዎች በበኩላቸዉ 9ኛ ተጠሪ በሚስነት ድርሻቸዉ እና ሌሎች ተጠሪዎች ደግሞ ባለን በወራሽነት ድርሻ የሚደርሳንን የአክስዮኖችን ድርሻ በእያንዳንዳችን ስም ተመዝግቦ በማህበራቱ በአባልነት ሊንመዘገብ ይገባል እንጂ በጋራ አንድ እንደራሴ ወክለን በዉክልና እንዲንጠቀምበት የሚያስገድደን የመተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌም ሆነ የንግድ ሕግ ድንጋጌ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡
ከዚህ አንጻር የአመልካቾች ማህበራት ኃላፊነታቸዉ የተወሰኑ የግል ማህበራት እንደመሆናቸዉ መጠን መታየት ያለበት የንግድ ሕጉ አንቀጽ 510 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሆናቸዉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ሕግ አንቀጽ 510 ሥር

እንደተመለከተዉ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ትርጎም ጸባይ ምን እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን፣ ይህ ማህበር የሚያስከትለዉ የኃላፊነት መጠን እና የአባላቱ ቁጥር ምን ያህል መሆን እንዳለበት እና የሚተላለፉ የንግድ ወረቀቶችን ማዉጣት እንደማይችል ተመልክቷል። እንዲሁም በሕጉ አንቀጽ 524 መሰረት ደግሞ በዚህ ማህበር ያለዉን የአክስዮን ድርሻ ለወራሽ በምን አግባብ እንደሚተላለፍ የሚደነግግ ነዉ። የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደሚያመለክተዉ በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ በሌላ አግባብ ካልተመለከተ በቀር የአንድ ማህበርተኛ ወራሾች ለሟቹ አክስዮኖች በደንብ ወራሾች እንደሚሆኑ ይደነግጋል። እንግዲህ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በተመለከተ አንድ የማህበሩ አባል የሞተ እንደሆነ የሟቹ የአክስዮኖች ድርሻ በምን አግባብ ወደ ወራሾች እንደሚተላለፍ የማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ እና የዚህ ሕግ ድንጋጌ መሰረት የሚፈጸም መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ስለማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ እንዳመለከተዉ አንቀጽ 4.4 የጋራ ባለአክስዮኖች መብታቸዉን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸዉ የሚያመለክት እና መብታቸዉን ለአንድ ሰዉ በመወከል መጠቀም እንደሚችሉ እንደሚደነግግ ነዉ። ሌላዉ የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 3.1 ድንጋጌ ደግሞ የወራሽነት መብት ያለዉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይዞ የቀረበ ወራሽ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ የማህበራቱ አባል የሚሆንበትን የሚያረጋግጥ መሆኑን እንደሚያመለክት ገልጾዋል። ይህን የንግድ ሕጉን ድንጋጌ እና የመተዳደሪያ ደንቡን ድንጋጌ በጣምራ ሲታይ የማህበራቱ አባል በሞት የተለየ እንደሆነ በማህበራቱ የነበረዉ የአክስዮን ድርሻ ለወራሾች የዉርስ መብታቸዉን መሰረት በማድረግ እንደሚተላለፍ የሚደግፍ እንጂ ምንም ዓይነት ክልከላ የሌለዉ መሆኑን ነዉ። ይህ ከሆነ ደግሞ ሟች አቶ አለሙ ገብሩ በአመልካቾች ማህበራት የነበራቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ ለአሁን 9ኛ ተጠሪ እና ለሌሎች ተጠሪዎች በምን አግባብ ሊተላለፍና ሊጠቀሙበት እንደሚገባ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ።

ከዚህ አንጻር የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት ክርክር ተጠሪዎች በማህበራቱ ዉስጥ መብት ያገኙባቸዉን አክስዮኖችን በምን አግባብ እንደሚጠቀሙበት የማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 4.4 እና የንግድ ሕጉ አንቀጽ 328 ድንጋጌ መሰረት ሲታይ አንድ ሰዉ በመወከል ሊጠቀሙ ይገባል እንጂ እያንዳንዳቸዉ የማህበራቱ አባላት መሆን አይችሉም ሲሉ፤ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ በማህበራቱ ዉስጥ ባገኘነዉ የአክስዮኖች ድርሻ መሰረት እያንዳንዳችን አባላት ሆነን ለመመዝገብ የሚከለክለን ነገር ስለሌለ በአባልነት ሊንመዘገብ ይገባል የሚለዉ ነዉ።

ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ኃለፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሁለት ዓይነት ባህርያት ያሉት ሲሆን አንዱ በአባላቱ መካከል ካለዉ ግንኙት አንጻር የሽርክና ማህበር ባህርይ እና ከሚያስከትለዉ ኃላፊነት አንጻር የኩባንያ ባህርይ ያለዉ መሆናቸዉ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል። ስለሆነም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚመለከቱት የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች የማይሸፍናቸዉ ጉዳዮች ካሉ እንደየአግባብነታቸዉ መታየትና ተፈጻሚ መደረግ የሚገባቸዉ የሽርክና ማህበር እና ኩባንያን የሚመለከቱት የንግድ ሕጉን ድንጋጌዎች መሆናቸዉን መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ።

በዚህ መሰረት የአሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ የማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ እና የንግድ ሕጉ አንቀጽ 328 ድንጋጌ ማየቱ ተገቢ ነዉ። ይህ የመተዳደሪያ ደንቡም ሆነ የንግድ ሕጉ ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ እንደሚያመለክተዉ የጋራ ባለአክስዮኖችን

የሚመለከቱ ናቸዉ፡፡ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 4.4 መሰረት የጋራ ባለአክስዮኖች ያላቸዉን መብታቸዉን ለአንድ ሰዉ በመወከል መጠቀም ከሚችሉ በስተቀር እያንዳንዳቸዉ የማህበሩ አባላት ሆኖ መመዝገብ እንደማይችሉ የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 328 [1] ድንጋጌ መሰረት አክስዮኖቹ የማይከፋፈሉ መሆናቸዉን የሚያመለክት ሲሆን፣ ንዑስ አንቀጽ 2 ደግሞ ብዙዎች ሰዎች የአክስዮኖች የጋራ ባለሀብት የሆኑ እንደሆነ የማህበርተኛነትን መብት ሊሰራባቸዉ እንዲችል ለሁሉም እንደራሴ የሚሆን መሾም አለባቸዉ በማለት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ መረዳት እንደሚቻለዉ ብዙ ሰዎች ብዙ አክስዮኖችንም ቢሆን ለእያንዳንዳቸዉ አንድ አንድ አክስዮን የማይደርሳቸዉ እንደሆነ ወይም አንድ አክስዮን በጋራ የያዙ እንደሆነ፣ እነዚህን አክስዮኖች ወይም አንዱን አክስዮን ለእያንዳንዱ የጋራ ባለአክስዮኖች ማከፋፈል የማይቻል ስለሆነ በጋራ መያዝ ስለሚገደዱ፣ እነዚህ ሰዎች መብታቸዉን መጠቀም የሚገባቸዉ አንድ ሰዉ በመወከል ከሚሆን በስተቀር እያንዳንዳለቸዉ በአባልነት መመዝገብ እንደማይችሉ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ ሟች ከአመልካቾች ማህበራት የነበሩት የአክስዮኖች ድርሻ አንጻር የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሚስትነት መብታቸዉ የሚደርሳቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ እና ከ1ኛ-8ኛ ተጠሪዎች ባላቸዉ የወራሽነት መብታቸዉ የሚደርሳቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ ሲታይ አክስዮኖቹ ሊከፋፈሉ የማይችሉ እና ተጠሪዎች ሰዉ በመወከል በጋራ ለመያዝ የሚገደዱበት አግባብ ያለ መሆኑን የሚያሳይ ነገር የለም፡፡ ምክንያቱም ሟች አቶ አለሙ ገብሩ በአመልካቾች ማህበራት የነበራቸዉ አክስዮኖች ብዛት ሲታይ ተጠሪዎች ባላቸዉ መብት አክስዮኖቹ ለእያንዳንዳቸዉ ተከፋፍለዉ በስማቸዉ ተመዝግቦ እነርሱም በማህበራቱ በአባልነት ለመመዝገብ የሚከለክላቸዉ ምንም ነገር የለም፡፡

ተጠሪዎች በእነዚህ አክስዮኖች ላይ ካላቸዉ መብት አንጻር ለእያንዳንዳቸዉ ተከፋፍለዉ ብይዙ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ እና የንግድ ሕግ ድንጋጌ የሚከለክላቸዉ አይሆንም፡፡ ሟች በእነዚህ ማህበራት የነበራዉ የአክስዮኖች ድርሻ ብዛት ለተጠሪዎች ባላቸዉ መብት ከመከፋፈል የሚከለክላቸዉ እና የጋራ ባለአክስዮኖች ሆኖ አንድ ሰዉ በመወከል መብታቸዉን እንዲጠቀሙበት የሚገደዱበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ሟች አቶ አለሙ ገብሩ በአሁን 1ኛ አመልካች ማህበር 9,136 አክስዮኖች ድርሻ እንደነበራቸዉ እና በአሁን 2ኛ አመልካች ማህበር ደግሞ 2,900 አክስዮኖች ድርሻ እንደነበራቸዉ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የአሁን 9ኛ ተጠሪ ከእነዚህ አክስዮኖች የሚስትነት ድርሻቸዉ በአሁን 1ኛ አመልካች ሟች ከነበራቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ ግማሹ የእሳቸዉ በመሆኑ 4,568 አክስዮኖች እንደሚደርሳቸዉ፣ በአሁን 2ኛ አመልካች ደግሞ ሟች ከነበራቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ ግማሹ 1,450 እንደሚደርሳቸዉ፤ ከ1ኛ-8ኛ ተጠሪዎች የሟች ወራሾች በመሆናቸዉ በ1ኛ አመልካች ከሚደርሳቸዉ አክስዮኖች ለእያንዳንዳቸዉ 571 አክስዮኖች እንደሚደርሳቸዉ እና በ2ኛ አመልካች ደግሞ ለአሁን 5ኛ ተጠሪ ለአቶ ዳንኤል አለሙ 183 አክስዮኖች እና ለሌሎች ተጠሪዎች ደግሞ 181 አክስዮኖች እንደሚደርሳቸዉ የሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪዎች የአክስዮኖች ድርሻቸዉ በአመልካቾች ማህበራት በአባልነት ከመመዝገብ የመተዳደሪያ

ደንብ ድንጋጌም ሆነ የንግድ ሕጉ ድንጋጌ የሚከለክላቸዉ ሆኖ አልተገኘም። በንግድ ሕጉ አንቀጽ 534 [2] ሥር እንደተመለከተዉ እያንዳንዱ ማህበረተኛ በማህበሩ ዉስጥ ባሉት አክስዮኖች ልክ የድምጽ ብዛት እንዳለዉ ከደነገገዉ አንጻር ሲታይ ተጠሪዎች በየስማቸዉ በማህበራቱ በአባልነት የተመዘገቡ እንደሆነ፣ ድምጽ የሚሰጡት ባላቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ መጠን ስለሆነ በአመልካቾች ላይ የሚያመጠዉ ችግር መኖሩን የተመለከተ ነገር የለም። እንዲሁም የማህበራቱ አባላት ብዛትም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 510 [2] ሥር ከተመለከተዉ ቁጥር በላይ እስካልሆነ ድረስ፣ በዚህ ረገድም ችግር ይፈጥራል ተብሎ አይገመትም። በመሆኑም ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 [3፣ ሀ] እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር ቅሬታም ሆነ አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የማያመልክት ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል።ከዚህ አንጻር ይህ ችሎት በሰ.መ.ቁ.41526 [ቅጽ 9] ግንቦት 2 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ችሎቱ የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ለማየት ስልጣን እንደሌለዉ የወሰነዉን ማየት ይቻላል።

ሲጠቃለል የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ባላቸዉ መብት መሰረት በአመልካቾች ማህበራት እያንዳንዳቸዉ በስማቸዉ በሚደርሳቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ መጠን በአባልነት ተመዝግበዉ የመጠቀም መብት አላቸዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ በሕግ አግባብ የተሰጠ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል።

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.169919 በ12/07/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት ጸንቷል።
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

**መዝገቡ ተዘግቷል።**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ